

አቡ ሙሐመድ አልተስቱሪ እንዲህ ይላሉ፡-

«መልካም ሥራዎችን መልካም ሰዎችም ሆኑ መጥፎዎቹ ሊሠሯቸው ይችላሉ። ወንጀልን የሚርቁት ግን እውነተኛ የአላህ ባሮች ብቻ ናቸው።»

እናም የሐራም እይታን መራቅህ ወደ እውነተኞቹ ደረጃ ከፍ ያደርግሃል። የኔ ሚና ለዚህ የሚረዱህ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። ቀጠልኩ፡-

1. አነፃዕር

አቡ ዒስማህ እንዲህ ይላሉ፡- «በአንድ ወቅት አላህ ይዘንላቸውና ዚንኑን አልሚስሪ ዘንድ ነበርኩ። አንድን የሚያምር ወጣት በማስተማር ላይ ነበሩ። አንዲት ውብና በስነ-ምግባሯ የምትታወቅ ሴት ድንገት አለፈች። ወጣቱ ሰረቅ አድርጎ ተመለከታት ይህንን ያስተዋሉት ዚንኑን የወጣቱን አንገት ጠምዘዝ አደረጉና እንዲህ አሉት፡-

ላፈር ለውሃ ቆንጆ ልብህን አትማርከው

ለጀነቷ ሑረልዐይን ራስህን አውለው።

ከዛሬዎቹ ቆነጃጅት ላይ ዓይኑን መንቀል የተሳነው ሰው ከነገዎቹ የጀነት ቆነጃጅት ጋር ያነፃዕራቸው። ያኔ ልዩነቱን በትክክል ይረዳል። ሑረልዐይን ምን ማለት እንደሆነች ታውቃለህ? በውበቷ የፀሐይ ውበት ይደበዝዛል። ከፈገግታዋ የሚወጣው ነፀብራቅ ከሙብረቅ ብልጭታ የበለጠ ያበራል። ወደ ዱንያ ብቅ ብትል ሰማይ ምድሩን በመልካም ጠረኗ ባወደችው ነበር። የፍጡራን ድምፅ በተስቢሕ (ሱብሓነላህ)፣ በተህሊል (ላ ኢላሀ ኢለላህ) እና በተክቢር (አላሁ አክበር) ከአዕናፍ አዕናፍ ባስተጋባ ነበር። የፍጥረተ ዓለሙን አድማስ ባስዋበችው ነበር። የፀሐይ ብርሃን የከዋክብትን ብርሃን እንደሚውጠው ሁሉ የሷ ብርሃንም የፀሐይን ብርሃን ባጠፋው ነበር። በምድር ላይ ያለ ሰው ሁሉ አንድም ሳይቀር በኃያሉ አላህ ባመነ ነበር። የአካሏ ብርሃን ከሰባ ውብ ልብሶቿ ባሻገር ያንፀባርቃል። ከአካሏ በቀጥታ የሚመነጨው ብርሃኗ እንዴት ይሆን?! አላህ (ሱ.ወ.) የጀነት ሰዎች እንዳይሞቱ ባይወስን ኖሮ ከመጠን

ያለፈ ውበታን መቋቋም ተስኗቸው ህይወታቸውን ባጡ ነበር። ለባለቤታ ስትስቅ ጅንን በብርሃን ስለምትሞላ ሴት ምን ልልህ እችላለሁ?

ከአንድ የጅንት ቤተ መንግስት ወደ ሌላኛው ስትንቀሳቀስ ሀሀይ በምህዋሯ የምትሽከረከር ስለምትመስል ውብ ሴት ምን ትላለህ? ይህ ሁሉ እንግዲህ አንተ ከፍታ ለተፈጠረችዋ የዱንያ ቁንጅ ልብህ በጠፋበት ሁኔታ መሆኑ ነው። ሴሐራም ዕይታ የፈረምክ ወንድሜ ሆይ! ሁሉቱ እይታዎች አብረው አይሄዱም። ላሬ እይታውን ከፍታ የቆጠበ ሰው ነገ ሐረልዐይንን ማየት ይቻለዋል። ላሬ እይታውን ሴሐራም የተጠቀመበት ደግሞ የነገዋን ቁንጅ የማየት ዕድል አይኖረውም። ምርጫው ያንተ ነው። የሐረልዐይን ጥሎሽ ማትረብ የምትችልበት ዕድሉ አለህ። ጥሎሹን አቡደርዳእ (ረ.ዐ) ይነግሩሃል፡- «ከሐራም እይታ ዐይኑን የቆጠበ የፈለገውን ያህል ሐረልዐይን ይዳርለታል።»

2. ፍናቸውን ተከተል

የሰለፎችን መልካም ጠረን አሽትት። በታሪካቸው ጥምህን አርካ። እነሱን በማስታወስ ልብህን አንቃ። ምሰላቸው። ምናልባት እነሱን ለመምሰል መጣርህ እነሱኑ እንድትሆን ያስችልህ ይሆናል።

✓ ሪቢይዕ ኢብኑ ኸይሰም ይባላል። ከዐብዱላህ ኢብኑ መስዑድ (ረ.ዐ) ምርጥ ተማሪዎች መካከል አንዱ ነው። ዐይኑን ከሐራም እይታ የሚያቅብ ነበር። በአንድ ወቅት በርካታ ሴቶች ከፊት ለፊቱ በማለፍ ላይ ነበሩ። ሪቢዓይ ዐይኑን ወደ መሬት ዝቅ አድርጎ አላለፋቸው። ሴቶቹ ማየት የተሳነው የአካል ጉዳተኛ እንደሆነ አሰቡና እንዲህ ሲሉ ዱዓ አደረጉ፡- «ጌታችን ሆይ! ከዐይነ-ስውርነት ጠብቀን።»

✓ ሐሰን ኢብኑ አቢ ሲናን ለዒድ ሶላት አደባባይ ወጥተው ሲመለሱ ሰዎች እንዲህ አሏቸው፡- «እንደባሬው ዒድ የሴቶች ቁጥር በዝቶ አያውቅም።» ሐሰን በመገረም እንዲህ በማለት መለሱ፡- «ከአደባባይ ወደ ቤቱ እስከመለስ ባለው ጊዜ አንዲትም ሴት አላገኘሁም።»

✓ ዳውድ ኢብኑ ዐብደላህ በወቅቱ በነበረው የበስራ አማር ይታደኑ ስለነበር አንድ ወዳጃቸው አስጠጋቸው። እቤቱም አስጠለላቸው። ሰውዬው ዘርቃኣ የምትባል በጣም ቁንጅ ሚስት ነበረችው። እንግዳውን በደንብ ትንከባከብና ታዋራው ዘንድ አደራ ብሏት ወደ ሥራው ሄደ። ከሥራው

ሲመለስ ዳውድን ጠየቃቸው፡- "ዘርቃእን እንዴት አገኘሃት? እንክብካቤዋስ እንዴት ነበር?" አላቸው። "ዘርቃእ ማን ነች?" አሉት። "ባለቤቱ ነች" አላቸው። «ዘርቃእ ትሁን ከህላእ» እኔ አላውቅም። «ፈዕሞ እንዲህ የምትባል ሴት አላየሁም» አሉት። ሰውዩው ወደ ባለቤቱ አመራና፡- «በደንብ ተንከባከቢው ብዬሽ አንቺ ግን ምንም ያደረግሽው ነገር የለም» አላት። «ዐይነ-ስውር ሰው ነው ተንከባከቢው ያልከኝ። በአላህ እምላለሁ አንድም ጊዜ ዐይኑን ወደ እኔ አላዞረም።»

✓ ሙሐመድ ኢብኑ ሲሪን ያሉትን እጅግ በጣም አስገራሚ ንግግር ደግሞ ላጫውትህ፡- አተኩሬ በህልሜም ሆነ በውኔ ከኡሙ ዐብደላህ ውጭ ማንንም ባዕድ ሴት አይቼ አላውቅም። (ኡሙ ዐብደላህ ባለቤታቸው ናት።) አንዳንዴ በህልሜ አንዲትን ሴት አይና የማትፈቀድልኝ ሴት መሆኗን አስታውሼ ዐይኔን ከእርሷ አዞራለሁ።»

ቀደምት ደጋግ ሰዎች በህልም እንኳ ለሚያዩዋት ባዕድ ሴት ዓይናቸውን ይቆጥባሉ። ይህ በእርግጥም አስገራሚ ነገር ነው።

እንዲህ ዓይነት ስብዕናዎች ዕዱዕ ስብዕናዎች ናቸው። ንዕህናቸው ልክ ኩልል እንዳለ የምንጭ ውሃ ነው። በክብር፣ በገንዘብና በሌላም መታመን የሚያስችል የሞራል ልዕልናን የተቆናጠጡ ምርጥ የአላህ ባሮች ናቸው።

3. ራስህን በጥሩ ምግባር ጥመድ

ነፍስህ ከመሮጥ አትደክምም፤ ከመንቀሳቀስ አትቆጠብም፤ ከሥራ አትቦዝንም። በመልካም ነገር ካልጠመድካት በአልባሌ ጉዳዮች ትተበትብሃለች። ለልዕልና ካላጨሃት የበታችነትን ታከናንብሃለች። የትጋቱ ባቡር ካመለጣት የስንፍናውን ትሳፈራለች። ጠንከር ባለ ገመድ መታሰር ያሻታል። ገመዱን ካጠበቅከው በሸሪዓ ሥርዓት ትታነፃለች። እስሩን ካላላኸው ግን ልክ እንደ እባብ መሹለክለኳ አይቀሬ ነው። ለነፍስህ አንድ ሥራ ምረጥ። ለአዕምሮህ አንድ ግብ አስቀምጥ። አካላትህ የሚለፋለት ቁምነገር ይፈልጋል።

ታላቁ ዑመር ኢብኑል-ኸጣብ (ረ.ዐ) ከነኚህ እውነታዎች በመነሳት ሥራ-ፈትነት የሰውን ልጅ መቀመቅ የሚከት በመሆኑ እንደሚጠሉት ገልፀዋል፡-

«ማናችሁንም የዱንያ ወይም የአኺራ ሥራ ላይ የሌለ ሥራ-ፊት ሆኖ ማየት አልፈልግም።»

ኢብኑል ቲይም የሰውን ልጅ ነፍስ አስመልክቶ የሰጡትን ትንታኔ ተመልከት፡-

«አላህ (ሱ.መ) የሰውን ልጅ ነፍስ ሲፈጥር ከወፍጮ ጋር አመሳስሎታል። ይህ ወፍጮ ያለማቋረጥ ይፈጫል። ጠቃሚ ጥራጥሬም ይሁን አፈርና አሸዋ የተጨመረለትን ሁሉ ይፈጫል። ነፍስ ውስጥ የሚብሰለሰሉ አስተሳሰቦች ወፍጮው ቂት ውስጥ እንደሚጨመር ግብዓት ናቸው። ይህ ወፍጮ ሥራ መፍታትን አያውቅም ምንጊዜም ያለማቋረጥ የሚጨመር ግብዓት ይፈልጋል። ጥቂት ሰዎች ወፍጮው ውስጥ የጥራጥሬ ግብዓት ይጨምሩና ለነርሱም ለሌላውም የህብረተሰብ ክፍል የማጠቅም ዱቄት ያመርታሉ። በአንዛሩ በርካታ ሰዎች የወፍጮው ቂት ውስጥ አሸዋ፣ ጠጠርና ብናኝ ይጨምሩና ይፈጫሉ። የማበክያውና የመጋገሪያው ሰዓት ሲደርስ የፈጩት ነገር ምንነት ይገለጽላቸዋል።» (አል-ፈዋኢድ)

መላኢካ ቂቱ ውስጥ የሚጨምረው ጠቃሚ ጥራጥሬ ሲሆን ሸይጧን ደግሞ አፈርና ጠጠርን ነው። በእርግጥ ሸይጧን ይህንን ማድረግ የሚችለው ወፍጮው ጠቃሚ ጥራጥሬ ከመፍጨት ከተዘናጋና ባለቤቱ ችላ ካለው ብቻ ነው። ሥራ-ፈት-የ ካገኘው በፍጥነት በራሱ ግብዓት ይሞላዋል።

4. ደመነፍሳዊ ስሜትን ሊያጠፋ የሚያስችል የአላህ ፍራቻ ይኑርህ

ደመነፍሳዊ ስሜት ተቀጣጣዩ ነው። አላህን የመፍራት ውሃ እንጂ ሊያጸናንው የሚችል ሌላ ነገር ፊዕሞ የለም። የፍርሃቱ ደረጃ ልቡ ሲገኝ የሸህዎን (የስሜትን) እሳት ያጠፋዋል። በውጤቱም ዐይን ከሐራም ይታቀባል። የፍርሃቱ ደረጃ ገበተኛ በሆነባቸው ሁኔታዎች የሸህዎ እሳት ይበልጥ ይጋጋማል። በውጤቱ ዐይን ለሐራም እይታ ይጋለጣል። ህሊና ያለው ሰው የእሳቱን ጥቃት መነሻ ሊያስተውል ግድ ይለዋል። ቃጠሎው ልብን በጠቅላላ አዳርሶ የከረፋ ሽታ ከመከሰቱ በፊት ሊረባረብ ይገባዋል። አላህ (ሱ.መ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلِمَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ جَنَّتَانِ ﴾ الرحمن: ٤٦

«በጌታውም ፊት መቆምን ለፈራ ሰው ሁለት ገነቶች አሉት።»

(አር-ረሀማን፡ 46)

ይህንን አንቀጽ አስመልክተው መጅሊድ የሚባሉ ታላቅ ዓሊም «ወንጀል ለመሥራት አስቦ አላህ ፊት መቆሙን አስታውሶ ወንጀሉን ከመፈፀም የተቆጠበን ሰው ለማመልከት ነው» ብለዋል።

ዐብደድ አብነ ዐመይር ታላቅ ታቢዒይ ነበሩ። በዘመናቸው «የመነጠው መነረ» በመባል ይታወቃሉ። ሶሓቦች እንኳ ሳይቀሩ በዚህ ታላቅ ሰው የምነር መድረክ በመገኘት ተግሳፃቸውን ያዳምጡ ነበር። ልባቸው ተነክቶ ያለቅሱም ነበር። ይህ ሰው ሸይጧንን በቱየጥር ስር ያዋለ፣ ለአላህ ባለው ፍራቻ ሸህዋውን ያሸነፈ ነበር። በዙሪያው ላሉት ሰዎች የሚያስተላልፈው ክልብ የመነጨ መልእክቶች ለበርካቶች ወደ አላህ መመለስ ምክንያት ሆነዋል። ከመነ ዘፋኝ ሴት ጋር የነበረውን ገጠመኝ እነሆ፡-

መነ ውስጥ የምትታወቅ አንዲት ቆንጆ ሴት ነበረች። ባለትዳር ነች በመስታወት መልኳን ተመልክታ በውበቷ ተደመመች። ባለቤቷን «ውበቴን አይቶ የማያፈተን ወንድ ይኖር ይሆን?» ስትል ጠየቀችው። «አዎ» ሲል መለሰላት። «ማን?» ስትል ጠየቀች። ዐብደድ አብን ዐመይር እንደማይፈተን ነገራት። ሴትዮዋም «ፍቃድህ ይሁንና ልፈትነው» አለችው። «ፊትደልሻለሁ» አላት። ይዛኔ ወደ መስጂደል ሐራም (የመነ መስጂድ) አመራች። ሃይማኖታዊ ብይን (ፈትዋ) እንደምትፈልግ ገለፀች። ከመስጂዱ ወደ አንድ ጥግ ገለል ብሎ ጥያቄዋን ሊያዳምጥ ተዘጋጀ – ዐብደድ አዚነ ዐመይር። ድንገት እንደጨረታ የሚያበራ ፊቷን ገለጠች። «አንች የአላህ ባሪያ ሆይ! አላህን ፍሪ» አላት። «በአንተ ፍትር ተፈትኛለሁ። እባክህን እንደሚሆን አድርግ» ስትል የፊተናዋን ጦር ሰነዘረች።

"ጥያቄ እጠይቅሻለሁ በእውነት ከመለስሽልኝ መሆን ያለበትን አደርጋለሁ" አላት።

"የምትጠይቀኝን ሁሉ በእውነት እመልሳለሁ" ስትል አረጋገጠች።

"የሚት መላኢካ ሩሕሽን ለመውሰድ ቢመጣ አሁን ከኔ የፈለግሽውን ጉዳይ መፈፀሜ ያስደስትሻል?"

"እረ በፍፁም!" ስትል መለሰችለት።

"እውነት ተናገርሽ" አላት ዐብይድ።

"ቀብር ውስጥ ገብተሽ ለጥያቄ በምትቀርቢበት ጊዜ አሁን ከኔ የፈለግሽውን ጉዳይ መፈፀሜ ያስደስትሻል?" ሲል አስከተለ።

"በፍፁም አያስደስተኝም" አለች።

"እውነት ብለሻል" አላት።

"ስምች የሥራ መዝገባቸውን በሚሰጡበት ጊዜ አንቺ የሥራ መዝገብሽን በቀኝሽ ይሁን በግራሽ የምተቀበይው ባላወቅሽበት ሁኔታ አሁን ከኔ የፈለግሽውን ጉዳይ መፈፀም ያስደስትሻል?" አላት።

"በፍፁም አልፈልግም" አለች።

"እውነት ብለሻል" አለ ዐብይድ።

"የቂያማ ቀን የሥራ ሚዛን ሲቀርብ የሥራሽ ውጤት ምን እንደሆነ ባላወቅሽበት ሁኔታ አሁን ከኔ የፈለግሽውን ጉዳይ መፈፀሜ ያስደስትሻል?"

"አልፈልግም ፊዕሞ አያስደስተኝም" አለች።

"አላህ ፊት ለጥያቄ እንደተረብሽ አስቢና ያኔ አሁን ከኔ የፈለግሽውን ጉዳይ መፈፀሜ ያስደስትሻል?"

"በፍፁም አያስደስተኝም" አለች።

"እውነት ብለሻል" አላት።

ዐብይድ ኢብኑ ዑመይር ከዚህ የጥያቄ ምልልስ በኋላ "አንች የአላህ ባሪያ ሆይ! አላህን ፍሪ በእርግጥ አላህ በርካታ ውለታን ውሎልሻል" በማለት ምክር ለገሣት።-

ይህች ሴት ወደ ባለቤቷ ተመለሰች። ባሏም ምን እንደፈፀመች ጠየቃት። "አንተ የማትረባ ነህ። ሁላችንም እርባና ቢሦች ነን" አለችውና ወደ ሶላት፣ ፆምና ዓባዳ ፊቷን አዞረች። የቁንጅዋን የሁኔታ ለውጥ ያየው ባለቤቷ "ዐብይድ ኢብኑ ዑመይር ምን አድርጌው ይሆን?! ባለቤቴን አበላሽብኝ። በየሌሊቱ ለእኔ መሽራ ነበረች። አሁን ግን ባህታዊ

ሠነች" ሲል የቁንጅዋን ሴት ነስሐ መግባትና ወደ አምልኮ መመለስ ይገልጻል።

የአላህ ፍራቻ የተለያዩ የአምልኮ ተግባራት ፍሬዎች ድምር ፍሬ ነው። ቁርአንን መቅራት ማብዛት፤ የቁርአንን ትርጉምና መልእክት ማስተንተን፤ ስለቲያማ ቀን ሁኔታ በየልቅ ማወቅ፤ የጀሀነምንና ባለቤቶቿን ሁኔታ ማስተንተን፤ አላህን የሚፈሩ ሰዎችን መሳዳትና ምክራቸውን ማድመጥ፤ ከአላህ መንገድ የተዘናጉ ግለሰቦችን ታሪክ ማወቅና ከነርሱም ራስን ማራቅ፤ አስክሬን ማጠብ፤ ጀናዛን መሸኘት፤ ለሞት የሚያጣጥሩ ሰዎችን ሁኔታ ማስተዋል፤ የምትፈፅማቸውን የአምልኮ ተግባራት ትንሽ አድርገህ መቁጠር፤ የአላህን ታላቅነት መገንዘብ፤ የአላህን ስሞችና ባህሪያት ማስተንተን... እነዚህና መሰል አምልኮቶች ሁሉ የአላህን ፍራቻ በውስጣችን ይፈጥራሉ።

5. ያምን አዘውትር

የስሜትና የትዕግስት መሠረቱ አንድ ነው። ከምግብ ስሜት መታገስ የቻለ ሰው ለመልካም ተግባር ያለው ተነሳሽነት ይበረታል። ከሐራም ዕይታ ስሜትም የመታገስ አቅም ይኖረዋል። ለዚህም ነው የፆም መልካምነት በተደጋጋሚ የተገለፀው። ፆመኛ ሰው ከፍላጎቱና ከእንስሳዊ ግፊቱ በፈቃዱ መታቀቡን ይማራል። ያ የውስጥ ስሜታዊ ግፊት በየትኛውም ጊዜ ድንበር ጥሶ እንዳያጠቃው ይከላከላል። እናም ዐይንን ከሐራም እይታ ማቀብ ቀጥተኛ ውጤት ይሆናል። ለዚህም ነበር ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) ጋብቻን መፈፀም ያልቻሉ ወጣቶችን እንዲህ በማለት የመከሩት፡-

((فعليه بالصوم فإنه له وجاء)) (البخاري ومسلم)

"በፆም አደራ! እሱ (ማግባት ለማይችል ሰው) ስሜትን ቀራጭ ነውና።"[1]

6. የጠላትህን ሴራ ጠንቅቀህ እወቅ

ሸይጣን ከልብ ጋር ያለው ፍልሚያ ፈርጀ ብዙ ነው። የትግል ሜዳውም ሰፊ ነው። ከሸይጣን ስልቶች ዋነኛው በሃያት ልብን ማጥቃት ነው። ይህም ግቡን ማሳካት ያስችለዋል። ከዚያ በኋላ የሱ ተከታይና

---

1 ቡኻሪና ሙስሊም

ወታደር እንድትሆን ያደርግሃል። አንድ ሺ ማይል በአንድ አርምጃ እንደማጀመር ሁሉ ይህም የጥሩት ጉዞ በአንድ የሐራም እይታ ይጀምራል።

ታላቁ ዓሊም ኢብኑል-ጀውዚ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ያብራሩታል፦

«በመጋለብ ላይ ያለች ፈረስ ደንበራ መንገድ በመሳጂ ምክኒያት የተመለሰ አካሏ ጠባብ ሸለቆ ውስጥ ሲሰነቀር በዓይነ-ህሊናህ አስብ። ቦታው ጠባብ ከመሆኑ የተነሳ ጋላቢው ከፈረሷ ላይ መውረድ አልቻለም። በዙሪያው ያሉ ሰዎች ፈረሷ መሉ ለመሉ ወደ ጠባቡ ሸለቆ ከመግባቱ በፊት ጋላቢው በፍጥነት ወደ ኋላ ይመልስ ዘንድ በከፍተኛ ድምፅ ያሳስቡታል። ጋላቢው ማሳሰቢያውን ተቀብሎ በፍጥነት አንድ አርምጃ ወደ ኃላ ከመለሳት ሁኔታው ይስተካከላል። በአንዛሩ ግን ጋላቢው በመዘግየቱ ምክንያት ፈረሷ ወደ ጠባቡ ሸለቆ መሉ ለመሉ ከገባ በኃላ የሚደረገው ጥረት አይጠቅምም። ጭራዋን ይዞ ከኃላ በኩል መጎተትም አጉል ድካም ነው። ምናልባትም ፈረሷን ካለችበት ሁኔታ ለማውጣት የማይቻል ይሆናል።»

ሐራም እይታ ልብ ውስጥ ሲያርፍ ምሳሌው ይህ ነው። ግለሰቡ በቆራጥነትና በፍጥነት ዐይኑን ከመለሰ፣ ከመጀመሪያው ጉዳዩን የቆረጠ ከሆነ ህዘምናው ቀላል ነው። እይታውን ከደጋገመና የሐራሙን ምስል ባዶ ወደ ሆነው ልቡ በማሸጋገር ከቀረፀ ውጤቱ አደገኛ ይሆናል። ተከታታይ እይታው የሸህዋን ዛፍ በተከታታይ ውሃ እንደማጠጣት ነው። ልብን በማበላሸትም ይቋጫል። አስተማሪነትን ከታዘዘበት ምህዳር አስወጥቶ ባለቤቱን ለአደጋ ይዳርገዋል። እጅግ ሀያሉ የሆነን ተግባር በማስፈፀም ግለሰቡን ለጥፋት በመዳረግ ይደመደማል።

7. የትዳርን ጣጣ ከቻልክ አግባ

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፦

((يا معشر الشباب من استطاع منكم الباءة فليتزوج، فإنه أغض للبصر وأحصن للفرج))

"እናንተ ወጣቶች ሆይ! ጣጣውን የቻለ ሁሉ ያግባ። ጋብቻ ዐይንን ከሐራም እይታ፣ ብልትን ከዝሙት ይጠብቃልና።"[1]

---

[1] ቡኻሪና ሙስሊም

የሐራም እይታን ፋና ሊያከሽፍ የሚችል ፍቱን መድሃኒት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ይጠቁማሉ። መድሃኒቱ ባለትዳሮችን ይመለከታል። ጃቢር (ረ.ዐ) እንዲህ ይተርከዋል፦

"የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አንዲትን ሴት ተመለከቱ። ወደ ዘይነብም አመሩ። ዘይነብ ሊጥ በማበሳት ላይ ነበረች። ጠሯትና ጉዳያቸውን ፈፀሙ። ከዚያም ወደ ሶሓቦቻቸው መጡና እንዲህ አሉ፦

((إن المرءة تقبل في صورة شيطان وتدبر في صورة شيطان فإذا أبصر أحدكم امرءة فليأت أهله فإن ذالك يرد ما في نفسه))

"ሴት ልጅ ፊት ለፊት ስትመጣም ይሁን ፊቷን አዙራ ስትሄድ ሸይጧን በሷ ይመሰላል። (እጅግ በጣም ትስባለች)። ከእናንተ ውስጥ አንዲትን ሴት የተመለከተ ባለቤቱ ጋር ይገናኝ። ይህ ነፍሱ ውስጥ ያለን (ስሀበት) ያስወግድለታል።"[1]

አማም አን-ነወዊይ፦ "ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን ያደረጉት ሶሓቦቹ መሰል ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ማድረግ ያለባቸውን ነገር በታልም በተግባርም ለማብራራት ነው" ብለዋል።

ምናልባት የአንድ ሰው ስሜት ድንገት ሊቀጣጠል ይችላል። የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ምክር ተግባራዊ በማድረግ ባለቤቱን በመገናኘት ካልሆነ መረጋጋት አይችልም ይሆናል። ለዚህም ነው ያለ በቂ ምክንያት ባለቤቷን ጥራሽ የምትከለክለን ሴት አስመልክተው ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከባድ ማስጠንቀቂያ ያስተላለፉት።

((إذا باتت المرءة مهاجرة فراش زوجها لعنتها الملائكة حتى ترجع))

«አንዲት ሴት የባለቤቷን ጥራሽ ትታ ካደረች ወደ ጥራሿ እስክትመለስ ድረስ መላእክት ይረግሟታል።»[2]

8. አላህ የምትሠራውን ሁሉ እንደሚያውቅ አስታውስ

አላህ (ሰ.ወ.) እንዲህ ይላል፦

((يَعْلَمُ خَائِنَةَ الْأَعْيُنِ وَمَا تُخْفِي الصُّدُورُ))

"(አላህ) የዐይኖችን ክዳት፣ ልቦችም የሚያብቱትን ሁሉ ያውቃል።" (ጋፊር:19)

---

1 ሙስሊም፣ አህመድና አቡዳውድ

2 ሙስሊም

ኢብኑ ዐባስ (ረ.ዐ) ይህችን አንቀጽ አስመልክተው እንዲህ ነበር ያሉት፡-

"አንድ ሰው ከጓደኞቹ ጋር ባለበት እንዴት ቆንጆ ሴት ታልፋለች። ዐይኑን ከርሷ እንዳቀበ ያስመስላል። ጓደኞቹ ትኩረታቸው ወደርሱ እንዳልሆነ ሲያስብ ዐይኑን ወደ ቆንጆዋ ይልካል። ጓደኞቹ የነቁበት ከመሰለው ዐይኑን ይመልሳል። ይህ ግለሰብ የሴትዮዋን ያልተፈቀደለት ገላ የመመልከት ፍላጎት እንዳለው የልብን ሚስጥር አዋቂ የሆነው ጌታ አላህ (ሱ.ወ) ያውቃል።"

ይህ ሚስኪን ሰው አላህን ያታለለ እየመሠለው ያታለለው ራሱን ነበር። ወንድሜ ሆይ! ሙራቀባ (ዘወትር በአላህ እይታ ሥር እንደሆኑ ማሰብ) ባህሪህ ሲሆን በውስጥህ በጎ ስሜት ይፈጠራል። የአላህ እይታ ከአንተ የሐራም እይታ የበለጠ ቅርብ እንደሆነ ይሰማሃል። ምክንያቱም እርሱ ከዋናው የደም ቧንቧህ ይበልጥ ቅርብ ነውና። መላኢኮቹ በቀኝም በግራም ቆመዋል። ስራህ ይመዘገባል፤ እይታዎችህ ይታደናሉ፤ ልብህ ላይ የምታስባቸው ሃሳቦች ሳይቀሩ ይከተባሉ፤ ይቀረሃሉ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፡-

وما كان ربك نسيا

"ጌታህም ረሺ አይደለም።" *(መርየም: 64)*

የምእመናን መሪ ዑመር ኢብኑ ዐብዱልዐዚዝ (ረ.ዐ) ሴት ልጅ ከአልማዝ ፈርጥ የተሰራ የአንድ ጆሮ ጌጥ ነበራት። ለአንዱ ጆሮዋ የሚሆን ተመሳሳይ ጌጥ ስላልነበራት ከሙስሊሞች የንብረት መጋዘን (በይተልማል) ተመሣሣይ የጆሮ ጌጥ ይልክላት ዘንድ ወደ አባቷ መልእክተኛ ላከች። ዑመር ሁለት የእሳት ፍሞች ላኩላትና እንዲህ በሏት አሉ፡- "እነዚህን ሁለት ፍሞች ጆሮዎችሽ ላይ ማድረግ ከቻልሽ ለአንዱ ጆሮሽ ከአልማዝ የሆነን ጌጥ እልክልሻለሁ።"

እኛም የአምስተኛውን ታላቅ ኸሊፋ መዝሃብ (መንገድ) በመከተል እንዲህ እንልሃለን፡- ‹አንተ ዐይንህን ለሐራም እይታ የለቀቅክ ወንድሜ ሆይ! በሁለቱ ዐይኖችህ ላይ ሁለት ፍም እሳቶችን ማስቀመጥ ከፈቀድክ ዐይኖችህን የሚያማምሩ ቆነጃጂት ላይ አሳርፋቸው።›